# እንደ ቤተሰብ



# እግዚአብሔርን በማወቅ እንዴት እናድጋለን

# መግቢያ

ህይወት ጉዞ ነው። እግዚአብሔር ይወድሀል፤በዚህ በህይወት ጉዞ ውስጥ ስኬታማ እንድትሆን ይፈልጋል።ስኬት አንተን ጨምሮ በማንኛውም ሰው ህይወት ውስጥ አስደናቂውን የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትህ በመፈጸም ወይም ባለመፈጸም ይወሰናል።በመረጥከው መንገድ ላይ በመሆን፤በዘለዓለማዊ መንግስቱ ውስጥ የተትረፈረፈውን በረከት እየተካፈልክ ልትፈጽም ትችላለህ ወይም በአንጻሩ ማለቂያ በሌለው ቅዠት ውስጥ ትኖራለህ።ብሩህ የሆነውን መንገድ መርጠህ የእግዚአብሔርን ዓላማ ትፈጽም ዘንድ በየዕለት ህይወትህ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ይኖርብሀል።ለዚህ ነው ይህ የመማሪያ መጽሐፍ አንተን ለመርዳት የተዘጋጀው።

እያንዳንዱ ሦስት የትምህርት ክፍሎች አሉት: {1}የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤ {2}መሠረታዊ ጥያቄዎች፤እና {3}የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ ናቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በማወቅ እንድታድግ ይረዱሀል።መሠረታዊ ጥያቄዎች ደግሞ በምታውቀው የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንድትኖር ይረዳሀል።የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ የቃሉን እውነት በልብህ እንድትሰውር ይረዳሀል።

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ እግዚአብሔርን የሚፈራ/የምትፈራ ወንድ ወይም ሴት፣እግዚአብሔር እንደ ሀሳቡ እና ፈቃዱ ይኖሩ ዘንድ የሚፈልጋቸው ባል ወይም ሚስት፤እንዲሁም ልጆችዎ እግዚአብሔርን እያወቁ ያድጉ ዘንድ እንዴት እንደሚረዷቸው፤ሳያገቡ ወይም ጃንደረባ ሆነው እንዴት እንደሚኖሩ እና እግዚአብሔርን ለቤተሰብዎ አባላት እንዴት ማካፈል እንደምትችሉ ለማወቅ መረዳትዎን በሚገባ ለማሳደግ ይረዳዎታል።

እያንዳንዱን ትምህርት በጸሎት ጀምር።መልሶቹን በራስህ አገላለጽ ጻፋቸው።በተገለጠልህ እውነት በሚገባ ትመላለስ እና ትኖር ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ። እግዚአብሔር እሱን በማወቅ ይባርክህ።

<u>ማስታወሻ</u>: አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መደበኛ ትርጉም መጠቀም ለዚህ የስልጠና አነስተኛ መጽሐፍ የተሻለ ነው።

# ትምህርት 1
# ወንድ
## *(ወንድ መሆን)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** *ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።*

1. ወንድ የተፈጠረው በማን አምሳያ ነው? ዘፍ 1:26-27

2. ለወንድ የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድ ነበር? ዘፍ 1:28; መዝ 115:16, 8:5-8

3. ወንድ የሰራው ለዚህ ዓላማ እንቅፋት የሆነ ነገር ምንድ ነበር? ዘፍ 3

4. ሰው ሰይጣንን አሸንፎ የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወቱ እንዴት ሊፈጽም ይችላል?
 1 ዮሐ 1:9, 5:4-5; ማቴ 6:33; ዮሐ 1:29; ራዕይ 12:10-11

5. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የእሱን ዓላማ በህይወታቸው ይፈጽሙ ዘንድ እንዲረዳቸው የሰጣቸው ስጦታ ምንድ ነው? ኤፌ 4:8; ሮሜ 12:6, 11:29

6. ሰው የተሰጠውን ስጦታ በሚገባ ይጠቀምበት ዘንድ ጥበብን እንዴት ያገኛል? ምሳ 1:7, 9:9-10,13:20; ያዕ 1:5

7. ሰው በህይወቱ የተሰጠውን ስፍራ እንዴት ያገኛል? ምሳ 18:16

8. ሰው እግዚአብሔርን እንዲያገለግል የተሰጠውን ስጦታ በአግባቡ ካልተጠቀመበት በፍጻሜው ምን ይሆናል?
 ማቴ 25:14-30

9. የሰውን ህይወት የሚመራው ማን ነው? ምሳ 16:9

10. ስለ ህይወት የሰው ልጅ አመለካከት ምን መሆን አለበት? መክብብ 3:22, 2:24-26

11. ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዴት ተዛምዶ እና ተስማምቶ መኖር አለበት? 1 ዮሐ 4:7, ገላ 5:13-14,
1 ጢሞ 5:1-2

12. እግዚአብሔር ባስተማረን መንገድ ሌሎችን ስንወድ ምን ይሆናል? ሮሜ 12:21

13. በእግዚአብሔር ኃይል ክፉን የማሸነፍ ውጤቶች ምንድ ናቸው? ራዕይ 21:7

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: (ለወንዶች ብቻ) በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. በእግዚአብሔር አምሳያ እንደተፈጠርክ አድርገህ እራስህን ትመለከታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, እግዚአብሔር ይህንን እውነት ለልብህ እንዲያበራልህ ጠይቅ፡፡

2. ልብህን ለኢየሱስ ሰጥሀልን እንዲሁም የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትህ ለመፈጸም ትኖራለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ይህንን ጸሎት ከልብህ ጸልይ፡፡

   "እግዚአብሔር አባት ሆይ, በኢየሱስ ስላሳየኸኝ ፍቅር አመሰግንሀለሁ፤ታስፈልገኛለህ፡፡ እኔ ከሰይጣን እና ከዓለም ተመልሻለሁ፤ልቤን ከፍቼ ስለሐጢያቴ ንስሀ እገባለሁ፤ኢየሱስ ሆይ ስለ ሐጢያቴ እንደሞትክ እና ከሞት እንደተነሳህ አምናለው፡፡ወደ ልቤ ግባ ነፍሴንም አድናት፡፡የህይወቴ ተቆጣጣሪ፤አዳኝ እና ጌታ ሁን፡፡በአንተ እኖር ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ሙላኝ፡፡ጸሎቴን ስለሰማኸኝ አመሰግንሀለሁ፤በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ፡፡አሜን."

3. እግዚአብሔር ለአንተ የሰጠውን ስጦታ አግኝተሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,እግዚአብሔር ይህንን እውነት እንዲያሳይህ ጠይቅ፡፡

4. እግዚአብሔር ለህይወትህ ያዘጋጀውን የጸጋ ስጦታዎች ከመፈለግ ይልቅ ያልሆንከውን ለመሆን ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ, አሁን እግዚአብሔር ትፈልግ ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

5. እግዚአብሔር ለአንተ ባለው ዓላማ ደስተኛ ነህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን በምስጋና የተሞላ ልብ እንዲሰጥህ ጸልይ፡፡

6. የእግዚአብሔርን ፍቅር በአካባቢህ ለሚኖሩ ሰዎች በማሳየት በዚህ ዓለም ያለውን ክፋት ለማሸነፍ ትፈልጋህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

**ማስታወሻ**: <u>መዝ 115:16 </u>በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡



ሰው ለኢየሱስ ሲኖር እግዚአብሔር በሚሰጠው በረከት ደስተኛ ይሆናል

# ትምህርት 2
# ሴት
# *(ሴት መሆን)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ሴት የተፈጠረችው በማን አምሳያ ነው? ዘፍ 1:26-27

2. የእግዚአብሔር ዓላማ ለሴቶች ምንድ ነበር? ዘፍ 1:28, 2:18

3. ሴት የሰራችው ለዚህ ዓላማ እንቅፋት የሆነ ነገር ምንድ ነበር? ዘፍ 3

4. ሴት ሰይጣንን አሸንፋ የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወቷ እንዴት መፈጸም ትችላለች?
   1 ዮሐ 1:9, 5:4-5; ዮሐ 12:29; ራዕይ 12:10-11; ማቴ 6:33

5. እግዚአብሔር ሴቶች የእሱን ዓላማ በህይወታቸው ይፈጽሙ ዘንድ እንዲረዳቸው የሰጣቸው ስጦታ ምንድ ነው? 1 ቆሮ 11:3, 6, 8-11; 1 ጢሞ 2:11-14; ኤፌ 4:8

6. ሴት የተሰጣትን ስጦታ በሚገባ ትጠቀምበት ዘንድ ጥበብን እንዴት ታገኛለች?
   ምሳ 1:7, 9:10, 31:30; ያዕ 1:5; ቲቶ 2:3-5

7. ሴት በህይወቷ ስፍራዋን እንዴት ታገኛለች?
   ምሳ 14:1, 31:31; ማቴ 26:6-13; ሐዋ 9:36

8. በእግዚአብሔር ጥበብ የማትኖር ሴት ምን ትመስላለች?
   ምሳ 14:1, 9:13-17, 30:20; 2 ጢሞ 3:6

9. በሐጢያት ህይወት ውስጥ የምትኖር ሴት ፍጻሜዋ ምን ይሆናል? ምሳ 10:27-30, 13:9

10. እንደ እግዚአብሔር ቃል ለምትኖር ሴት የተሰጣት የተስፋ ቃል ምንድ ነው? ምሳ 3:5-8

11. ስለ ህይወት የሴት ልጅ አመለካከት ምን መሆን አለበት? ፊሊ. 4:4-7

12.ሴት ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዴት ተዛምዳ እና ተስማምታ መኖር ይኖርባታል? 1ዮሐ 4:7, ገላ 5:13-14, 1 ጢሞ 5:1-2

13.እግዚአብሔር ባስተማረን መንገድ ሌሎችን ስንወድ ፍጻሜው ምን ይሆናል? ሮሜ 12:21

14.በእግዚአብሔር ኃይል ክፉን የማሸነፍ ውጤቶች ምንድ ናቸው? ራዕይ 21:7

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: (ለሴቶች ብቻ) በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. በእግዚአብሔር አምሳያ እንደተፈጠርሽ አድርገሽ እራስሽን ትመለከቻለሽን? አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አይደለም ከሆነ, እግዚአብሔር ይህንን እውነት ለልብሽ እንዲያበራልሽ ጠይቂ።

2. ልብሽን ለኢየሱስ ሰጥተሻልን እንዲሁም የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትሽ ለመፈጸም ትኖሪያለሽን? አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አይደለም ከሆነ,ይህንን ጸሎት ከልብሽ ጸልይ።

   "እግዚአብሔር አባት ሆይ, በኢየሱስ ስላሳየኸኝ ፍቅር አመሰግንሀለሁ፤ታስፈልገኛለህ። እኔ ከሰይጣን እና ከዓለም ተመልሻለሁ፤ልቤን ከፍቼ ስለሐጢያቴ ንስሀ እገባለሁ፤ኢየሱስ ሆይ ስለ ሐጢያቴ እንደሞትክ እና ከሞት እንደተነሳህ አምናለው።ወደ ልቤ ግባ ነፍሴንም አድናት።የህይወቴ ተቆጣጣሪ፤አዳኝ እና ጌታ ሁን።በአንተ እኖር ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ሙላኝ።ጸሎቴን ስለሰማኸኝ አመሰግንሀለሁ፤በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ።አሜን."

3. እግዚአብሔር የሰጠሽን ቤተሰብ በመርዳት የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትሽ ለመፈጸም ትኖሪያለሽን? አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አይደለም ከሆነ,እግዚአብሔር ይህንን ታደርጊ ዘንድ እንዲረዳሽ ጸልዪ።

4. እግዚአብሔር ለሴት የሰጠውን ጥሪ ከመቀበል እና ከወንድ እኩል ያለውን ዘለዓለማዊ ብድራት ከመረዳት ፈንታ በሁከት እንደ ወንድ ለመሆን ትፈልጊያሽን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አዎ ከሆነ,ንስሀ ግቢ፤በህይወትሽ ውስጥ እግዚአብሔር የሰጠሽን ሚና የሚቀበል ልብ እንዲሰጥሽ ፀልዪ።

5. እግዚአብሔር ለአንቺ ባለው ዓላማ ደስተኛ ነሽን? አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን በምስጋና የተሞላ ልብ እንዲሰጥሽ ጸልዪ።

6. የእግዚአብሔር ፍቅር በአካባቢሽ ለሚኖሩ ሰዎች በማሳየት በዚህ ዓለም ያለውን ክፋት ለማሸነፍ ትፈልጊያለሽን? አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አይደለም ከሆነ,
   ንስሀ ግቢ፤እግዚአብሔር እንዲረዳሽም ጸልይ።




ሴት ሌሎች የሚያስፈልጋቸው ነገር ይሟላ ዘንድ ለማገልገል በተጠራችበት መጠራት ትባረካለች

**ማስታወሻ**: ዘፍ 2:18. በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት ይሰውሩ።

# ትምህርት 3
# ባል
## (እግዚአብሔር የሚፈራ ባል እንዴት መሆን ይቻላል)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ሚስትን ስለ ማግኘት እግዚአብሔር ምን ይላል? ምሳ 18:22

2. እግዚአብሔር ጋብቻን እንዴት ይመለከታል? ማቴ 19:4-6

3. ክርስቲያን ማግባት ያለበት ማንን ነው? 2 ቆሮ 6:14-15

4. ባል በቤተሰብ ውስጥ ያለው ስፍራ ምንድ ነው? ማቴ 5:23

5. ባል ስለ ሚስቱ ያለው ኃላፊነት ምንድ ነው?
   ኤፌ 5:25, 28-29, 33; ቆላ 3:19; 1 ቆሮ 7:3; 1 ጴጥ 3:7

6. በጋብቻ ውስጥ ስላለ ወሲብ የእግዚአብሔር አስተምዕሮቶች ምንድ ናቸው? ዕብ 13:4, 1 ቆሮ 7:4-5

7. ቤተሰብ የሚያስፈልገውን ነገሮች ከማቅረብ አንጻር የባል ሃላፊነት ምንድ ነው?
   1 ጢሞ 5:8

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** (ለባሎች ብቻ) በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ሚስትህን ከእግዚአብሔር እንደተሰጠህ ውድ ስጦታ አድርገህ ትመለከታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን እሷን ከእግዚአብሔር የተሰጠህ ውድ ስጦታ አድርገህ መመልከት እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ።

2. ለቤተሰብህ አባላት ዘውትር በመጸለይ እና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በሟሟላት እንደ ቤተሰብ ራስነትህ አላፊነትህን ትወጣለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር የቤትህ

ራስ እንድትሆን እንዲረዳህ ጸልይ።

3. እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ሚስትህን እያከበርክ እና የሚያስፈልጋትን ነገር እያሟላ ትወዳታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ እግዚአብሔር ይህንን ማድረግ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ እየጠየክ ጸልይ።
4. ለጋብቻ ቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር አሁን ታማኝ ባል መሆን ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

5. የቤተሰብህን መንፈሳዊ፤ስሜታዊ፤አዕምሯዊ በተጨማሪም ስጋዊ እና ቁሳዊ ነገር ለማሟላት ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር ቤተሰብህን በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ማገልገል ትችል ዘንድ እንዲረዳህ እየጠየክ ጸልይ።

**ማስታወሻ:** <u>ኤፌ 5:25</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።
መልካም ባል እና አባት ስለመሆን በይበልጥ ለመረዳት <u>**ተጨማሪ መግለጫ ለ** አንብብ</u>።

ባል ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቱን ሊወድ ይገባል



# ትምህርት 4
# ሚስት
## (እግዚአብሔርን የምትፈራ መልካም ሚስት እንዴት መሆን ይቻላል)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. እግዚአብሔር ጋብቻን እንዴት ይመለከታል? ማቴ 19:4-6

2. ክርስቲያን ማግባት ያለበት ማንን ነው? 2 ቆሮ 6:14-15

3. ሚስት በግንኙነት ውስጥ ለባልዋ ማድረግ ያለባት ምንድ ነው?
   ኤፌ 5:22, 24; ቆላ 3:18; 1 ጴጥ 3:1-6

4. እግዚአብሔርን የምትፈራ ሚስት ቤተሰቧ የሚያስፈልገውን ነገር ከማቅረብ አንጻር ኃላፊነቷ ምንድ ነው?
   ምሳ 31:10-28

5. ይህ ከባሏ ጋር በሚኖራት ግንኙነት ውስጥ እንዴት ተጽዕኖ ሊያሳድርባት ይችላል? ምሳ 12:4

6. በጋብቻ ውስጥ ስላለ ወሲብ የእግዚአብሔር አስተምዕሮቶች ምንድ ናቸው? ዕብ 13:4, 1ቆሮ 7:4-5

7. እግዚአብሔር ልጆችን ስለማፍራት ምን ይላል? 1ጢሞ 2:15, መዝ 113:9

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: (ለሚስቶች ብቻ) በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ለክርስቶስ እንደሚሆን ለባልሽ በሚገባ ትታዘዢያለሽን? አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አይደለም ከሆነ፤ለባልሽ ትታዘዢ ዘንድ እንዲረዳሽ እና ጥበብና ጸጋ እግዚአብሔር እንዲሰጥሽ ጸልዩ።

2. እንደ ሚስት እና እናት ኃላፊነቶችሽን በሚገባ ትወጫለሽኝ? አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር እውነተኛ ክርስቲያን ሚስት እና እናት ትሆኚ ዘንድ እንዲረዳሽ ጸልዩ።

3. አንዱ የህይወት ጥሪሽ አካል እናት ለመሆን እና ምድር በሰው ትሞላ ዘንድ ለመርዳት ነውን? (ዘፍ 1:28) አዎ __ አይደለም __ መልስሽ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር በዚህ ዙሪያ ግልጽ የሆነ መረዳት እንዲሰጥሽ ጸልዩ፡፤

***የግርጌ ማስወታሻ***: አንዱ የሰው ልጅ ስህተት ዓለም እጅግ ቁጥሩ በበዛ ህዝብ ተጥለቅልቃለች የሚል ነው።እውነቱ ግን ሁሉም በዓለም ላይ የሚኖር ሕዝብ በአሜሪካ ውስጥ ከሚገኘው ለማንኛውም ትልቅ ከተማ ተመጣጣኝ መሆኑ ነው።ማንኛውንም ሰው ሊመግብ የሚችል ምግብ ከበቂ በላይ አለ፤ለዚህ ነው አሜሪካ ለገበሬዎቿ እህል እንዳያመርቱ የምትከፍለው።

***ማስታወሻ***: ኤፌ 5:22 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።



ሚስት ባል የሕይወት ግቡን ያሳካ ዘንድ ልትረዳው ይገባል

# ትምህርት 5
# ወላጅነት
## *(ልጆችን እንዴት እናሳድጋለን)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ልጆችን የሚሰጠን ማን ነው? መዝ 127:3-5

2. የአባት ኃላፊነት ለልጆች ምንድ ነው? ኤፌ 6:4, ቆላ 3:21, ኢያሱ 24:l5

3. የእናት ኃላፊነት ለልጆች ምንድ ነው? ቲቶ 2:4, ምሳ 31:27

4. ልጆች እግዚአብሔርን እንዲያውቁ እንዴት እናስተምራቸዋለን? ዘዳ 6:3-9, 11:18-21

5. ልጆች ለኢየሱስ መኖርን እንዳይማሩ የሚያግዳቸው እንቅፋቶች ምንድ ናቸው እንዴትስ እናስወግዳቸዋለን? ምሳ 22:15, 23:13-14, 13:24, 19:18, 29:15

6. ለልጆቻችን ልናደርገው የምንችለው በጣም አስፈላጊው ነገር ምንድ ነው? ማር 10:14

7. ልጆቻችንን እንደ እግዚአብሔር ቃል ስናሳድግ እግዚአብሔር የሰጠን የተስፋ ቃል ምንድ ነው? ምሳ 22:6

8. ልጆቻችንን የእግዚአብሔርን ቃል የማናስተምር ከሆነ ፍጻሜው ምን ይሆናል? ምሳ 29:15

9. ለኢየሱስ የምትኖር ከሆነ አንተ ለልጆችህ ምን ትሆናለህ እነሱስ ለአንተ ምን ይሆናሉ? ምሳ 17:6

10. ለኢየሱስ የምትኖር ከሆነ ልጆችህ ምን ይቀበላሉ? ምሳ 13:22

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: (ለወላጆች ብቻ) በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ልጆቻችሁን ከእግዚአብሔር እንደተሰጣችሁ ውድ ስጦታ አድርጋችሁ ትመለከታላችሁን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን ይህንን እውነት ለልብዎ እንዲያሳይዎ ይፀልዩ።

2. እንደ እናት ወይም አባት ወላጅ የሚጠበቅባችሁን ኃላፊነት በአግባቡ ተወጣላችሁን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን እንደ ወላጅ ኃላፊነታችሁን በአግባቡ መወጣት ትችሉ ዘንድ እንዲረዳችሁ ጸልዩ።

3. መንፈሳዊ የእግዚአብሔር ነገሮች ከልጆቻችሁ ጋር የምትነጋገሩበት ዋንኛ የየዕለት ጉዳይ ነውን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግቡ፤እግዚአብሔር የቃሉን እውነት ከልጆቻችሁ ጋር ትነጋገሩ ዘንድ እንዲረዳችሁ ጸልዩ።

4. ልጆቻችሁ በማይታዘዙበት ጊዜ በፍቅር ስርዓት ታስይዟችኋላችሁን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግቡ፤እግዚአብሔር ልጆቻችሁን በመንፈሳዊ ስርዓት ማሳደግ ትችሉ ዘንድ እንዲረዳችሁ ጸልዩ።

5. በልጆቻችሁ ህይወት ላይ አሁን የምታደርጉት ነገር ለወደፊት ማንነታቸው እጅግ ወሳኝ እንደሆነ ታውቃላችሁን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን ይህንን እውነት ለልብዎ እንዲያሳይዎ ፀልዩ።

6. ልጆቻችሁ ለክርስቶስ መኖር ይችሉ ዘንድ ልትረዷቸው ትፈልጋላችሁን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን ይህንን ለማድረግ እንድትችሉ እንዲረዳችሁ እና እንዲያሳያችሁ ጸልዩ።

**ማስታወሻ**: <u>ማር 10:14</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።
ስለወላጅነት የበለጠ ለማወቅ <u>**ተጨማሪ መግለጫ ሀ** ያንብቡ</u>።

ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው



# ትምህርት 6
# ልጅነት
## *(እግዚአብሔርን የሚፈራ መልካም ልጅ እንዴት መሆን እንችላለን)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. የእግዚአብሔር መንግስት ተካፋይ ለመሆን ምን መማር ይኖርብናል? ማር 10:15

2. በምን መንገድ ነው ሁልጊዜ ህጻናት መሆን ያለብን? 1 ቆሮ 14:20

3. የልጅ ኃላፊነት ለወላጆች ምንድ ነው? ኤፌ 6:1-3, ቆላ 3:20

4. ወላጆችህ እግዚአብሔርን እንዳትታዘዝ ቢጠይቁህ ምን ታደርጋለህ? ዘዳ 27:10; 30:19-20, ዳን1: 6-21

5. ልጆች ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ ከሆነ ምን ይሆናል? ምሳ 30:17

6. ልጅ እንደ ክርስቲያን ለመመላለስ ምን መፈለግ አለበት? 2 ጢሞ 2:22, 1 ጢሞ 4:12, መክብብ 12:1

7. እንደ ልጅ በምናድግበት ጊዜ ለወላጆቻችን ያለን ኃላፊነት ምንድ ነው? ምሳ 23:22, 1 ጢሞ 5:4

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: *(እግዚአብሔር የሚፈራ መልካም ልጅ እንዴት መሆን ይቻላል)*
በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. የልጅ ትሁት የሆነ የፍቅር አመለካከት አለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን እንዲሰጥህ ጸልይ።

2. በተቻለህ መጠን ወላጆችህን ማክበርና መታዘዝ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር አሁን ይህንን ማድረግ እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ።

3. እድሜ ሳይገድብህ የእግዚአብሔር ምሳሌ መሆን ትፈልጋህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር አሁን ይህንን ማድረግ እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ።

4. ለወላጆችህ የሚጠበቅብህን ሀላፊነት በመወጣት ቀጥለሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር አሁን ይህንን ማድረግ እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ።

**ማስታወሻ**: 1ኛ ቆሮ 14:20 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።




ለክፋት ባለን እውቀት ህጻናቶች ሆነን መኖር አለብን

# ትምህርት 7
## ያላገባ
## (በብቸኝነት መኖር)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አለማግባት ወይም በብቸኝነት ስለመኖር ምን ይላል? ማቴ 19:10-12; 1 ቆሮ 7:1,8,17,

2. ያለ ትዳር በብቸኝነት የመኖር ጥቅሙ ምንድ ነው? 1 ቆሮ 7:32, 34-35

3. ለምን አንድ ሰው ያለትዳር በብቸኝነት መኖር የለበትም? 1 ቆሮ 7:2, 9

4. ያላገባ ሰው በብቸኝነት መኖር አለበትን? መክብብ 4:9-12, መዝ 68:6

**መሠረታዊ ጥያቄዎች**: (ላላገቡ ብቻ) በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. እግዚአብሔር ሳታገባ እንድትኖር ጠርቶአልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ፤ጥሪህን ለመፈጸም እግዚአብሔር ኃይል እና ጥበብ እንዲሰጥህ ጸልይ።

2. የምትኖረው ብቻህን ነውን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ፤ከሌሎች ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ወይም ቤተሰብ የሆኑ የክርስቶስ ተከታዮች ጋር አብረህ የምትኖርበት በር እንዲከፍትልህ እግዚአብሔርን ፈልግ።

**ማስታወሻ**: 1ኛቆሮ 7፤17 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።



እግዚአብሔር ያላገባን ሰው
ቤተሰብ እንዲመሰርት ያደርገዋል

# ትምህርት 8
# የጾታዊ ግንኙነት ሥነ ስርዓቶች
## *(የእግዚአብሔር ግብረገባዊ ትምህርት)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. እግዚአብሔር ብልቶቻችንን ለምን ሰጠን? 1 ቆሮ 6:13-19

2. እግዚአብሔር ከጋብቻ በፊት ስለሚደረግ ወሲብ፤ዝሙት እና ወሲባዊ መመሰቃቀል ምን ይላል? ገላ 5:19-21, ኤፌ 5:5-7

3. የዝሙት ሐጢያትን ስንለማመድ ፍጻሜው ምን ይሆናል? 1 ቆሮ 6:18, ምሳ 6:26-29

4. ግብረገብ ስለሌላት ሴት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ምሳ 23:27-28, 9:13-18

5. ግብረገብ ስለ ሌለው ወንድ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ምሳ 6:32

6. አንድ ሰው የወሲብ ፈተናን እንዴት ማሸነፍ ይችላል? 1 ቆሮ 6:18, 2 ጢሞ 2:22, ያዕ 4:4-10

7. ወሲብ ትክክል የሚሆነው መቼ ነው? ዕብ 13:4

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ከጋብቻ ውጪ የሚደረግ ወሲብ እና ወሲባዊ ድርጊት ሐጢያት እንደሆነ ትረዳለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር ይህንን እውነት ለልብህ እንዲያበራልህ ጸልይ።

2. በህይወትህ ውስጥ ስላለው ተገቢ ያልሆነ የወሲብ አመለካከት እና ተግባር ንስሀ ገብተሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ንስሀ ግባ።

3. የዝሙት ፈተና ሲያጋጥምህ ትሸሻለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር አሁን ይህንን ማድረግ እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ።

ከዝሙት ምኞት
መሸሽ አለብን




**ማስታወሻ:** ዕብ 13፤4 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

# ትምህርት 9
# ጋብቻ እና ፍቺ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ስለ ፍቺ የእግዚአብሔር ሐሳብ ምንድ ነው? ሚል 2:16

2. እግዚአብሔር ፍቺን ለምን ይፈቅዳል? ማቴ 19:8

3. ባል ሚስቱን መፍታት ያለበት በምን አይነት ሁኔታ ነው? ማቴ 5:32

4. አንድ ሰው እንደገና ለማግባት ነጻ የሚሆነው መቼ ነው? ማቴ 19:9, 1 ቆሮ 7:27-28

5. ሚስት ባልዋን መፍታት ያለባት በምን አይነት ሁኔታ ነው፤እንደገና ማግባት ትችላለችን?
   1 ቆሮ 7:10-11, 39; ሮሜ 7:2

6. እግዚአብሔር ጋብቻ እና በፍቺን በተመለከተ ህግጋቱን የሚጥሱትን እንዴት ይመለከታቸዋል?
   ማር 10:11-12

7. ጋብቻ እና ፍቺን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ህግጋት በሚጥስ ማኅበረሰብ ላይ ውጤቱ ምን ይሆናል?
   ኤር 23:10, 5:7-9, 13:25-27, 29:22-23; ሆሴዕ 4:1-3

8. ጋብቻ እና ፍቺን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ህግጋት መጣሳችንን ስናውቅ ምን ማድረግ አለብን?
   1ቆሮ 7:17,24,27,10-11; 1 ዮሐ 1:9

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. ፍቺን ትጠላለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር እሱ እንደሚያየው እንድታይ፤እንዲሁም እሱ እንደሚጠላው እንድትጠላ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

2. ጋብቻ እና ፍቺን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላልፈሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ፤ንስሀ ግባ ትክክለኛውን ነገር እንድታደርግም ከልብህ ፈልግ፡፡

3. ጋብቻ እና ፍቺን በተመለከተ ለሌሎች የእግዚአብሔርን እውነት ባለማካፈል ወይም ከቃሉ ውጪ የሆነን ነገር በማካፈል የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዲጥሱ አድርገሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤ጋብቻ እና ፍቺን በተመለከተ እግዚአብሔር ለቃሉ እንድትኖር እና ቃሉን እንድትናገር እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

4. የፍቺ መርገም ከአገርህ እንዲወገድ ትጸልያልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን መጸለይ ጀምር፡፡

**ማስታወሻ:** ሚልኪያሥ 2፤16 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡




**እግዚአብሔር ፍቺን ይጠላል**

# ትምህርት 10
# የፈረሱ ቤቶች
## *(የፈረሱ ቤቶችን እንዴት እናቀናለን)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማስላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ከሚስቱ ጋር በፍቺ ለተለያየ ባል የእግዚአብሔር ሀሳብ እና ፈቃድ ምንድ ነው? ኤፌ 5:25, 2 ቆሮ 5:18-19, 1 ጢሞ 5:8

2. ከባልዋ ጋር በፍቺ ለተለያየች ሚስት የእግዚአብሔር ሀሳብ እና ፈቃድ ምንድ ነው? 1 ቆሮ 7:11,

3. እግዚአብሔር በሐጢያት ምክንያት ቤተሰብ የፈረሰባቸውን ሰዎች እንዴት ይመለከታቸዋል? ኤር 14:17

4. በቤተሰቦቻቸው ሁኔታ ልባቸው ለተሰበረባቸው ሰዎች የእግዚአብሔር መሻት እና ፈቃድ ምን ለማድረግ ነው? ቆሮ 147:3, ኢሳ 61:1

5. እግዚአብሔር የተሰበረውን ልባችንን እንዲጠግን እና ፍላጎታችንን እንዲሟላ ይረዳን ዘንድ ብንፈቅድለት በፍጻሜው ምን ይሆናል? መዝ 10:14, 146:9, 68:5; ኢሳ 54:5

6. የፈረሰውን ግንኙነታችንን በተመለከተ እራሳችንን ከምን መጠበቅ ይኖርብናል? ዕብ 12:15

7. ያለንበት ሁኔታ እንዲቀየር እና የተሰበረው ልባችን ይፈወስ ዘንድ የሚረዳንን ምን ነገር ማድረግ ይኖርብናል? ማቴ 5:44

8. ቤታችን የፈረሰ ከሆነ ስላለንበት ሁኔታ እናደርግ ዘንድ እግዚአብሔር የሚጠይቀን ነገር ምንድ ነው? 1 ቆሮ 7:26-27, 39-40; ፊሊ. 4:11-12; ያዕ 5:16

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. እግዚአብሔር የፈረሱ ቤቶች እንደገና እንዲጠገኑ እንደሚፈልግ ታውቃለህን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር ይህንን እውነት እንዲያበራልህ ጸልይ፡፡

2. ቤታቸው የፈረሰባቸው ወደ መታረቅ ይመጡ ዘንድ እግዚአብሔርን ከልባቸው እንዲያምኑ ታበረታታለህን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግ ጀምር፡፡

3. ሰዎች የተሰበረው ልባቸው ይጠገን ዘንድ ብቸኛው መንገድ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ብቻ ህብረት በመፍጠር እንደሆነ ታምናለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር እውነቱን እንዲያበራልህና ልባቸው የተሰበረባቸውን ታገለግል ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

4. ቤታቸው የፈረሰባቸውን ሰዎች መንፈሳዊ እና ስሜታዊ ፍላጎቶቻቸውን ያሟሉ ዘንድ ምድራዊ የሆነ ግንኙነት ከሚመሰርቱ ይልቅ ከኢየሱስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲመለከቱ ታበረታታለህን ? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግ ጀምር፡፡
5. ቤታቸው የፈረሰባቸው እግዚአብሔር ለጉዳታቸው ይቅርታን ከመላኩ በፊት ሁኔታዎቻቸውን ይፈቱ ዘንድ በጸሎት እንዲቆዩ እና የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ እንዲሟላላቸው እግዚአብሔርን እንዲታመኑ ታበረታታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግ ጀምር፡፡

**ማስታወሻ:** መዝ 147፤3 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡



**እግዚአብሔር የፈረሱ ቤቶችን ሊፈውስ ይፈልጋል**

# ትምህርት 11
# ያልዳኑ ወዳጆቻችን
## *(ኢየሱስን ከቤተሰብ ጋር እንዴት እንካፈላለን)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. በክርስቶስ ላልዳኑ ወገኖቻችን እግዚአብሔር የሰጠን የተስፋ ቃል ምንድ ነው? ሐዋ 16:31

2. በክርስቶስ ያልዳው ባለቤቷ ይድን ዘንድ ሚስት ማድረግ ያለባት ነገር ምንድ ነው?
   1 ጴጥ 3:1-2, 1 ቆሮ 7:13-16, ምሳ 22:6

3. በክርስቶስ ያልዳነችው ባለቤቱ ትድን ዘንድ ባል ማድረግ ያለበት ነገር ምንድ ነው?
   ኤፌ 6:4, 5:25; 1 ቆሮ 7:12, 14-16; ቆላ 3:19

4. ልጅ በክርስቶስ ያልዳኑ ወዳጆቹ ይድኑ ዘንድ ምን ማድረግ አለበት?
   ኤፌ 6:1-2, 1 ጢሞ 4:12

5. በክርስቶስ ካልዳኑ ሰዎች ጋር ስንኖር ችግሮችን ለመፍታት ምን ማድረግ እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ምን ይለናል? ሮሜ 12:17-21

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ለክርስቶስ የማይኖሩ የቤተሰብዎ አባላትን እግዚአብሔር እንደሚያድናቸው ታምናለህን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር ስለ እነሱ ደህንነት እምነት እንዲሰጥህ አሁን እየጸለይክ ጠይቅ።

2. እነሱ ለኢየሱስ ለክርስቶስ ይኖሩ ዘንድ ማድረግ የሚገባህን ነገር እያደረክ ነውን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር እነሱን ወደ ጌታ ኢየሱስ ለማምጣት የድርሻህን ማድረግ ትችል ዘንድ ጌታ እንዲረዳህ ጸልይ።
3. በየቀኑ ከእነሱ ስትወያይ የኢየሱስን ፍቅር ታሳያቸዋለህን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር ትወዳቸው ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

**ማስታወሻ:** ሐዋ 16፤31 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

ያልዳኑ የቤተሰባችን አባላት እኛ
ለኢየሱስ ስንኖር አይተው አምነው ይድናሉ፡፡



# ትምህርት 12
# የቤተሰብ የገንዘብ አያያዝ
## *(የገንዘብ አያያዝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህዎች)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ፡፡ ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው፡፡

1. የቤተሰብን ንብረት የመቆጣጠር ሀላፊነት ያለበት ማን ነው? 1 ጢሞ 5:8

2. ይህንን ለማድረግ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን እርዳታ እንዴት ያገኛል? ዘዳ 8:18, ማቴ 6:31-33, ፊሊ 4:19

3. ሴቶች የቤተሰባቸውን መሰረታዊ ነገር ከማሟላት አንጻር የሚኖርባቸው ሀላፊነት ምንድ ነው? ቲቶ 2:4-5, ምሳ 31:10-31

4. የእግዚአብሔር መንግስት ተካፋይ ለመሆን እና የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል አንድ ሰው ማድረግ ያለበት ነገር ምንድ ነው? ማቴ 4:17, 25:14-30; ሐዋ 3:19; 2 ጢሞ 1:9; ሮሜ 11:29; ኤፌ 5:17;

5. ስለ *ሥራ* አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባ አመለካከት ምንድ ነው? ኤፌ 4:28, 6:6-7

6. አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባ የ*ሥራ* ባህል ምንድ ነው? ምሳ 14:23, 13:11, 10:4&16

7. እግዚአብሔር ባርኮ በሰጠን ነገሮች ምን ማድረግ ይኖርብናል? ምሳ 3:9-10; ሚል 3:10-11; ማቴ 6:19-21; 1 ቆሮ 16:1-2; 2ቆሮ 8:12-15, 9:6-8

8 እግዚአብሔር አስራታችንን እናስገባለት ዘንድ የሚጠብቅብን የማከማቻ መጋዘን ምንድ ነው? ዘፍ 14:18-20, 1ቆሮ 9:9-11, ገላ 6:6, 1 ጢሞ 5:17-18

9. ከአስራታችን ባሻገር ሌላ የምንሰጠው ለማን ነው? ያዕ 2:15-16, 1ዮሐ 3:17, ገላ 6:10

10. በገንዘብ አያያዝ ማድረግ የሌለብን ነገር ምንድ ነው? ሮሜ 13:8; ምሳ 22:26, 17:18

11. እንደ 1 ጢሞ 6:6-10 ገለጻ ቁሳዊ ነገሮች ስለሚያመጡት ደስታ ወይም እርካታ ሊኖረን የሚገባ አመለካከት ምንድ ነው?

12. ገንዘብ ስናጠፋ መመሪያችን ምንድ ነው? 1 ቆሮ 10:31

13.እግዚአብሔር ቤተሰብ የሚያስፈልገውን መሰረታዊ ነገሮች ከማቅረብ አንጻር እንዳይረዳን የሚያደርገው እንቅፋት ምንድ ነው? ዘዳ 28:15-20

14. እንደ እግዚአብሔር ቃል የምንኖር ከሆነ በቤተሰባችን ላይ ምን ይሆናል? ዘዳ 28:1-13

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ቤተሰብህን ትረዳ ዘንድ ማድረግ የሚገባህን ነገር ትመለከታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፣አሁን ጸልይ፣እግዚአብሔርም እንዲያሳይህ ጠይቅ።

2. በህይወትህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ትፈልጋለህን፣የሚያስፈልግህን ሊሰጥህ እንደሚችል ታምናህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፣ንስሀ ግባ፣እንዲሁም እግዚአብሔር አሁን ማድረግ እንድትችል እንዲረዳህ ጠይቅ።

3. እግዚአብሔር በስራህ ይባርክህ ዘንድ ስለ ሥራ እና መልካም የስራ ባህል የተስተካከለ አመለከካት አለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፣እግዚአብሔር መልካም አመለካከት እና መልካም የሥራ ባህል ይኖርህ ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

4. ገንዘብህን በአግባቡ በመያዝ እግዚአብሔርን ታከብራለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ እንዲሁም እግዚአብሔር አሁን ማድረግ እንድትችል ጠይቅ።

**ማስታወሻ:** ፊሊ. 4፤19 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

$ ስለምናጠፋው ገንዘብ እግዚአብሔርን መጠየቅ አለብን

## ተጨማሪ መግለጫ ሀ
## ልጆችህን እግዚአብሔርን በማወቅ ያድጉ ዘንድ ሊታወሱ የሚገባቸው ነጥቦች

1. ለልጆችህ የምትሠጠው ምክር በመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች እና ወጥነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት እንጂ በወቅታዊ የማህበረሰቡ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ መሆን እንደሌለበት እርግጠኛ ሁን።

2. ለቤተሰብህ የምትወስነው ውሳኔ በመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች እና ወጥነት ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት እርግጠኛ ሁን።

3. **ለትምህርት ላልደረሱ እና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜ ላይ ለሚገኙ:** በእያንዳንዱ ምሽት መጽሐፍ ቅዱስ ወይም መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መጽሐፍ የምታነብላቸውን ጊዜ ወስን።ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ገጸባህሪያት እና ስለኑሯቸው አስተምራቸው።ኢየሱስ ማን ነው፤አትዋሽ፤አትስረቅ፤እንዲሁም እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ ውደድ የሚሉትን መሰረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ይረዱ ዘንድ ይርዷቸው። እንዲሁም፤የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክቶችን እና ቁልፍ ጥቅሶችን በሚገባ ያስታውሱ ዘንድ ያግዟቸው።

4. **ለአቅመ አዳም ያልደረሱ:** ቤተሰብዎ የሚሳተፉበት የቤተሰብ መንፈሳዊ ጉባዔ ይኑርዎት።በአንድ ቀን ቢያንስ አንድ ምዕራፍ እንዲያነቡ በመርዳት ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ እንዲያነቡ ጠይቋቸው።ስለ ግላዊ ህይወት፤የቤተሰብ ህይወት፤የቤተክርስቲያን ህይወት፤የወንጌል ስብከት እና ደቀመዝሙርነት ያለውን መሰረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች እንዲማሩ እና በህይወታቸው እንዲተገብሩ ይርዷቸው።በህይወት ትልቁ ስኬት እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ እንደሆነ እና የእሱን ዓላማ መፈጸም እንደሆነ ያስተምሯቸው።ያንን እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።እንዲሁም ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችን ያስታውሱ ዘንድ ይገባቸዋል።

# ተጨማሪ መግለጫ ለ

## መመሪያ ለባሎች እና ለአባቶች

(ቤትዎን ሰዎች *እግዚአብሔርን እያወቁ የሚያድጉበት* ስፍራ እንዴት እናደርጋለን)

1. የእግዚአብሔርን ዓላማ እንደያዝክ እና በህይወትህ የሱን ዓላማ ልትፈጽም እንደምትኖር እርግጠኛ ሁን።

2. እቅድህን ለሚስትህ እና ለቤተሰብህ አካፍል።ጸልይላቸው፤እንዴት እነሱ ተካፋይ እንደሆኑ ለማሳየት ለእግዚአብሔር የምትሰጠውን ጊዜ ወስን።

3. ሚስትህ እና ቤተሰብህ እግዚአብሔርን እያወቁ እንዲያድጉ እና በህይወታቸው የሱን ዓላማ እየፈጸሙ እንዲኖሩ ጸልይላቸው።

4. እግዚአብሔርን ለቤተሰብህ የወንጌል ተልዕኮ እቅድህ ጠይቅ።የምትጸልይለትን አንድ ሚሲዮናዊን ወይም የወንጌል አገልጋይ ተቀበል፤እንደ ቤተሰብም ድጋፍ አድርግ።

5. ቤተሰብህን በጸሎት እየመራህ፤ለጎረቤቶችህ፤ለጓደኞችህ እና ዘመዶችህ ምስክር በመሆን አገልግል።

6. እግዚአብሔር እንደመራህ ለወንጌል ተልዕኮ አገልግሎት ጉዞ ውጣ።

God has a wonderful purpose for your life. We want to help you find and fulfill that purpose.
If you would like further training, prayer, or information on how you can work with others to share about knowing God where you live; please contact us.


WRITE TO:

BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. BOX 633
Grapevine, TX 76099
U.S.A.

Phone (228) 255-9251

by Email
Send your request to basic@basicministries.com
Or
Visit our web site www.basicministries.com


IF YOU WERE BLESSED BY THIS BOOKLET SHARE A COPY WITH SOMEONE.
ADDITIONAL COPIES CAN BE DOWNLOADED FROM OUR WEB PAGE
http://www.basicministries.com

COPIES ARE AVAILABLE IN OTHER LANGUAGES.
CONTACT US FOR MORE INFORMATION.

WOULD YOU LIKE TO HAVE A HAPPY HOME?

WOULD YOU LIKE TO GET ALONG WITH YOUR RELATIVES?

WOULD YOU LIKE TO KNOW HOW TO RAISE CHILDREN?

WHAT ABOUT BEING SINGLE?

WANT TO KNOW HOW TO HEAL A BROKEN HOME?

!!THEN THIS BOOK IS FOR YOU!!

Compiled by Henry Pulsifer

&

Illustrated by Paula Mingucci

This is one of a series of booklets designed to help you *grow to know God* and fulfill His purpose for your life. Henry has experienced the victory that comes from knowing God for over 60 years; including God's healing from cancer as he walked with the cross. Since his healing he has traveled the world sharing *how to know God*; and helping others find blessings and success by *growing to know Him*, and fulfilling His purpose for their life.

Out of this experience he has compiled several learning guides that enable people to*grow to know God*, and understand how to live the basic Bible principles for blessings and success in life. This particular learning guide is designed to help you *grow to know God* through your family relationships by understanding and applying God's principles for family living. It can also be used to help you teach others, and is appropriate for individuals or groups.

COPYRIGHT 1990 ALL RIGHTS RESERVED
No part of this booklet may be reproduced without permission from the publisher.
Exception: portions may be reproduced if distributed free of charge.
Proper credit should be given for the source of the material.

PUBLISHED BY:

BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. Box 633
Grapevine, TX 76099
USA

Phone (228) 255-9251

Email basic@basicministries.com
On the web at www.basicministries.com